# "ፈረንጅ አምላኩ…" ማን ነው? ፫ኛ

ገ/ኢ. ጐርፉ

ከታወቀ የአዲስ አበባ ሆስፒታል ሲሠራ የነበረ አንድ ሓኪም ያጫወተኝን አልረሳውም። አብረውት የሚሠሩ ፈረንጅ አስታማሚዎች ነበሩት። ታድያ በተደጋጋሚ የደረሰብኝ ሁኔታ ነው እያለ፣ ሕመምተኞቹ፤ "ለምን ነጩ አያክመኝም?" "አንተ አትንካኝ!" "እሱ ይመርምረኝ" ሲሉኝ፣ "እሱማ አስታማሚ ነው፣ ዶክተሩ እኮ እኔ ነኝ" ብላቸው፣ "ግድ የለም፣ እሱ ነጭ ነው፣ እሱ ቢያክመኝ ይሻለኛል…" የሚሉ በዙዎች ነበሩ፣ ብሎ ነገረኝ።

ሌላም የቅርብ ቤተ-ዘመድ የሆኑ አዛውንት ወደ አሜሪካ መጥተው በመኪና ስንሸራሸር ከመንገድ አንድ ነጭ ለማኝ አዩና፤ "ነጩ! አሜሪካዊው! እንዴት ይለምናል!" በማለት ፈጽሞ ማመን አቃታቸው። "አባባ፣ ቆዳው ነጭ መሆኑ ምን ፋይዳ አለው? ማንም ሰው የሚረባ ትምህርት ሆነ ችሎታ ከሌለው ሠርቶ ሊበላ አይችልም። ያለው አማራጭ ታድያ ከመንገድ ቆሞ ልመና ብቻ ነው።" አልኳቸው። ቀኑን ሙሉና ሰሙኑንም በዚህ ሁኔታ ሲገረሙና ሲደነቁ ሰነበቱ። አገር ተመልሰውም ወሬያቸው ሁሉ ስለዚሁ ለማኝ ጉዳይ እንደ ነበር ሰማሁ።

ይህንና ይህን የመሳሰለ ነገር በሃገራችን ሰዎች ተደጋግሞ ሲፈጸምና ሲነገር ስናይ፣ "ሓበሻ ኩሩ ሕዝብ ነው፣ በኮሎንያሊዝም ስላልተጠቃ ለነጭ ሰው አያጎበድድም…" እያሉ አጉል ጉራ መንዛት ምን ፍሬ አለው? ሕመማችንን ማመንና መድሓኒትም በቶሎ መፈለጉ አይሻለንም ወይ?

በሃገራችን የባኅል ሚኒስተር መሥሪያ ቤትና ጽሕፈት ቤት አለ፣ ከዚህ ላይ ታድያ ሓላፊነቱና ተሳትፎው ምንድነው? የውጭ አገር ቋንቋና ትምህርት መማር እጅግ ጠቃሚ ነው፣ ግን ሌሎች የሰለጠኑ ሃገሮችን ብናይ የገዛ ራሳቸውን ባኅል እየተዉና እያንቋሸሹ እኮ አይደለም የሰለጠኑት። ከቻይናና ከጃፓን ማየትና መማር ይበጃል። የራሳችን የሆነውን ባኅል ብንመለከት ደግሞ ባኅላችን ሙሉ በሙሉ መልካም ነው ማለት አይደለም። በባኅላችንም የሚገኙ ተግባሮችን ሁሉ መመርመርና ደግ-ደጉን አጥብቀን መያዝ፣ የማይረቡትን ወይም የሚጎዱትን የባኅል ርዝራዦችን ደግሞ አርቀን ማስወገድ ይገባናል።

የዘመኑ ተማሪዎች ትምህርት በራሳቸው ቋንቋ መማር ስለሚጀምሩ የራሳቸውን ባኅል ለማጥናት ዛሬ አመቺ ጊዜና ሁኔታ ነው። ሰው በልጅነቱ ባኅሉን ይዞ ሲያድግ በራሱ ባኅል እንዲኮራ፣ ደጉንና ደግ ያልሆነውንም እንዲመረምር ዕድል አገኘ ማለት ነው። በራስ ባኅል መኩራት ከፈረንጅ አምልኮ ለመዳን ይረዳል። ቀጥሎም በቅን መንፈስ የራስን ባኅል አስተውሎ መመርመር፣ መርምሮም የማይረባውንና የሚጎዳውን ማስወገድ የሚገባ ነው።

**ይቀጥላል…**